የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 14.
ADDIS ABABA 16th March, 2020


**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፬/፪ሺ፲፬


የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ............ገጽ ፲፬ሺ፪


**Content**

Regulation No. 494/2022


Drivers Qualification Certification License Regulation ....................................Page 14002


## ደንብ ቁጥር ፬፻፺፬/፪ሺ፲፬

## የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲ አንቀጽ ፳፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፬/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "አዋጅ" ማለት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፸፬/፪ሺ፲ ነው፤

## REGULATION NO. 494/2022

## DRIVERS QUALIFICATION CERTIFICATION LICENSE COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 28 (1) of Drivers Qualification Certification License Proclamation No.1074/2018.

### PART ONE

### GENERAL

1. **Short title**

This Regulation may be cited as the "Drivers Qualification Certification License Regulation No. 494/ 2022".

2. **Definition**

Unless the context requires otherwise, in this Regulation:

1. "**Proclamation**" means a "Drivers' Qualification Certification License Proclamation No. 1074/2018" ;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price 31.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001



Scanned by CamScanner

፪/ **"ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ"** ማለት ባለሞተር ተሽከርሪዎች ለማሽከርከር የሚያስችል ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ለሁለት ዓመት እንዲያገለግል ተብሎ በፈቃድ ሰጪው አካል የሚሰጥ ጊዜያዊ ፈቃድ ነው፤

፫/" **አግባብነት ያለው አካል"** ማለት በክልሎች፤ በከተማ መስተዳድሮች ወይም በፌደራል ትራንስፖርትን ለመምራት እና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው፤

፬/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተጠቀሱት ትርጓሜዎች እንደ አግባቡ በዚህ ደንብ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

፭/ በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት
## አጠቃላይ ግዴታዎች

### ፫. ስለማሰልጠኛ ተሽከርካሪዎች

፩/ ማንኛውም ማሰልጠኛ ተቋም ሥልጠና የሚሠጥባቸውን ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች በየጊዜው በመፈተሽ ለሥልጠና ብቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤

፪/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በማንኛውም ጊዜ ማሰልጠኛ ተቋሙ ለማሠልጠኛነት የሚጠቀምባቸውን ተሽከርካሪዎችና ማሽነሪዎች ብቁነት መመርመር ይችላል፤

፫/ ለማሠልጠኛነት የሚውሉ ተሽከርካሪዎችን የእድሜ ገደብ፤ ቀለም፤ የተሽከርካሪ ወይም ማሽነሪ ዓይነት እና የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፎ በሚገኝ ማሠልጠኛ ተቋም ላይ ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2. **"Temporary Driving Qualification Certification License"** means temporary license issued by the licensing authority to permit the driving of motor vehicles for a period of two years prior to issuance of permanent drivers' qualification certification license;

3. **"Appropriate Organs"** means an organ of the Federal, Regional or City Administration responsible for administering and regulating road transport;

4. Definitions provided under Article 2 of the Proclamation shall also be applicable to this Regulation wherever appropriate;

5. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## PART TWO
## GENERAL OBLIGATIONS

### 3. Training Vehicles

1/ The training institution shall periodically inspect that the vehicles or machineries it employs for training are suitable and fit for the purpose;

2/ The Ministry or the appropriate organ may at any time inspect the vehicles and machineries used by the training institution for training;

3/ The Ministry shall determine through Directives the age, color and type of vehicles or machineries that may be used for training and other measures that may be taken against training institutions that fail to comply with the provisions of this Regulation.

Scanned by CamScanner

**፬. የማሰልጠኛ ተቋማት ግዴታዎች**

በአዋጁ የተቀመጡት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም የማሰልጠኛ ተቋም ሰልጣኙን ተቀብሎ ከማሰልጠኑ በፊት፦

፩/ የሰልጣኙ የትምህርት ደረጃ፣ እድሜ እና የጤና ሁኔታ መሟላታቸውን አረጋግጦ የመመዝገብ፣

፪/ ለሥልጠና የተመዘገበውን ሰልጣኝ በሥርዓተ ትምህርቱ እና በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የማሰልጠን፣

፫/ ሥልጠና ከመጀመሩ በፊት ለፈቃድ ሰጪ አካላት የሰልጣኙን ሙሉ መረጃዎች በተዘጋጀው ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ ወይም በመረጃ መረብ መላክ፣

፬/ ተሽከርካሪዎች ላይ የተገጠሙት ለስልጠና አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች መሟላታቸውን፣ መስራታቸውን እና ዓመታዊ የቴክኒክ ምርመራ ማድረጋቸውን በሥልጠና ወቅት የማረጋገጥ፣

፭/ በአግባቡ ሥልጠናቸውን ላጠናቀቁ እጩ ሰልጣኞች የምስክር ወረቀት የመስጠት፣

፮/ ብቃት ያላቸው አሰልጣኞችን በመቅጠር አሰልጣኞቹ በአግባቡ ሥልጠናውን በመስጠት ብቃት ያላቸውን ሰልጣኞች ብቻ ለፈተና ማቅረባቸው የመከታተል እና የመቆጣጠር፣

፯/ አግባብነት ባለው አካል በማንኛውም ጊዜ ሲጠየቅ የማሰልጠኛ ማሽነሪዎች ወይም ተሽከርካሪዎች ለምርመራ የማቅረብ፣

፰/ በሚኒስቴሩ በሚወሰነው የተሽከርካሪ የእድሜ ገደብ፣ የቀለም እና የተሽከርካሪ ዓይነት የማሰልጠን፣

4. **Obligations of Training Institutions**

Without prejudice the obligations stipulated in the Proclamation, any training institution shall have the following duties:

1/ Ensure that the educational, age and health requirements of the trainee are fulfilled before admitting the trainee;

2/ Deliver the training to the trainee in accordance with the curriculum and as the schedule set for such training;

3/ Forward through the pre-established reporting format detailed information of the trainee to the license issuing organs;

4/ Ensure during the training that all required instruments are installed; properly functioning and annual technical inspections are met on the vehicles by which the training is administered;

5/ Issue certificate to the trainees who successfully completed the training;

6/ Hire qualified trainers supervise and inspect that the trainers are properly delivering the training; and that only qualified trainees are screened for examination;

7/ Cause the inspection of training machineries or vehicles whenever so requested by the appropriate organ;

8/ Deliver the trainings with the defined age limit, color and category of vehicles as may be determined by the Ministry;

Scanned by CamScanner

፱/ ማንኛውም እጩ ሰልጣኝ ሥልጠናውን ጀምሮ ሳያጠናቅቅ በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥ ካቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ያለ ተጨማሪ ክፍያ ስልጠናውን የመስጠት፤

፲/ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የተግባር ሥልጠና መጀመሪያ በተመረጡ ቦታዎች፤ ቀጥሎም አነስተኛ የትራፊክ ፍሰት ባለባቸው በተመረጡ መንገዶች ላይ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## ፭. ስለ የንድፈ-ሀሳብ እና የተግባር ፈተና

### ፩/ የንድፈ-ሀሳብ ፈተና

ሀ) የንድፈ ሀሳብ ፈተና የወደቀ ተፈታኝ ውጤቱ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያለምንም ሥልጠና በተጨማሪ ሁለት ጊዜ የፈተና ዕድል ተሰጥቶት እንዲፈተን ይደረጋል፤

ለ) የንድፈ-ሀሳብ ፈተና አልፎ የተግባር ፈተና ለወደቀ ተፈታኝ የአንድ ጊዜ የንድፍ ሀሳብ ፈተና ውጤት ለአንድ ዓመት ብቻ ያገለግላል፡፡ ከአንድ ዓመት በኋላ ለሚመጣ ተፈታኝ የንድፈ-ሀሳብ ፈተና እንደገና እንዲወስድ ይደረጋል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) መሠረት የንድፈ ሀሳብ ፈተና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማለፍ ያልቻለ ሰልጣኝ ወደ ማሰልጠኛ ተቋም ሄዶ ሰልጥኖ እንደገና ለፈተና ይቀርባል።

9/ Where the trainee failed to complete the training for whatever reasons, deliver the training free of any additional charges for such trainee provided that the trainee applied for readmission within one year from the date the training was interrupted;

10/ Deliver practical trainings initially on designated areas, then on selected routes with low traffic as per requirements set by the Ministry.

## 5. Theoretical and Practical Examinations

### 1/ Theoretical Examination

a) A trainee who fails to pass theoretical examination is entitled to two more opportunities for reexamination provided that these two more opportunities are exploited by the trainee within one year from the date the first exam resulted is announced;

b) A passing result of a trainee on theoretical examination shall be valid for one year even if the trainee fails to pass the practical examination; where such one year period has lapsed the trainee shall retake the theoretical examination;

c) Where a trainee fails to pass theoretical examination as stated under Sub-Article (1) (a) of this Article, he shall attend the training institution before taking the re examination.

Scanned by CamScanner

፪/ **<u>የተግባር ፈተና</u>**

ሀ) የተግባር ፈተና የወደቀ ተፈታኝ ውጤቱ ከተገለፀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ውስጥ ያለምንም ስልጠና በተጨማሪ ለሦስት ጊዜ የፈተና ዕድል ተሰጥቶት እንዲፈተን ይደረጋል፤

ለ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የተግባር ፈተና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ማለፍ ያልቻለ ሰልጣኝ ወደ ማሰልጠኛ ተቋም ሄዶ ሰልጥኖ እንደገና ለፈተና ይቀርባል፤

ሐ)የመጀመሪያው የተግባር ፈተና የሚሰጠው ለዚህ ዓላማ ተለይቶ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል አስቀድሞ በተከለለ ስፍራ ወይም በተመረጠ መንገድ እና አነስተኛ የትራፊክ ፍሰት ባለበት በተመረጠ መንገድ ላይ ሆኖ ሚኒስቴሩ በሚደነግገው ርቀትና መስፈርት መሰረት ይሆናል፤

መ) አንድ ሠልጣኝ የተግባር ፈተና አለፈ የሚባለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪)(ሐ) ድንጋጌ መሠረት በተከለለው ስፍራ ወይም በተመረጠው መንገድ እና አነስተኛ የትራፊክ ፍሰት ባለበት የተመረጠ መንገድ ላይ የሚሰጡትን ሁለቱንም ፈተናዎች ካለፈ በኋላ ነው፤

፫/ በአንድ ማሠልጠኛ ተቋም ውስጥ በማንኛውንም የስልጠና አሰጣጥ ጉድለት ወይም የተቋሙ ችግር በሆነ ሌላ ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀፅ (፩) እና (፪) መሠረት የሚሰጡ ፈተናዎችን ሰልጣኞች በተደጋጋሚ የሚወድቁ ከሆነ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል በሚይዘው ሪከርድና ተጨማሪ ምርመራ መሠረት በማሰልጠኛ ተቋሙ እና በአሰልጣኙ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

2/ **<u>Practical Examination</u>**

a) A trainee who fails to pass practical examination is entitled to three more opportunities for reexamination provided that these three more opportunities are exploited by the trainee within one year from the date the first exam resulted is announced;

b) Where a trainee fails to pass practical examination as stated under paragraph (a) of this Sub-Article, he shall attend the training institution before taking the reexamination;

c) The practical examination shall be administered initially at designated compounds or selected roads for this purpose; and then on selected roads with low traffic flow as per the distance and standard prescribed by the Ministry;

d ) A trainee is said to have passed practical examination only when he passes both the examinations administered at the designated compound or selected places and on the selected road with low traffic as per Sub-Articles (2) (c) of this Article;

3/ The Ministry or the appropriate organ may take administrative measures against a training institution and a trainer where, based on records and further investigations, there is found a manifest number of trainees repeatedly failing examinations administered as per Sub-Articles (1) and (2) of this Article;

Scanned by CamScanner

፬/ ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ፈተና ወስደው ካለፉት ሰልጣኞች ውስጥ ናሙና በመውሰድ ብቃታቸውን በድጋሚ ፈተና ማረጋገጥ ይችላል፤

፭/ ሚኒስቴሩ ብቃት ሳይኖረው ፈተና እንዲያልፍ ያደረገ የማሽከርከር ብቃት አረጋጋጭ ባለሙያ፣ ፈቃድ ሰጪ አካል እና ያለአግባብ ያለፈው ሰልጣኝ ላይ አስተዳደራዊ የቅጣት እርምጃ ይወስዳል፤

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፭) መሰረት የሚወሰድ አስተዳደራዊ ቅጣት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፮. የጤና ሁኔታ

፩/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ሰው ከታወቀ የህክምና ተቋም ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ባዘጋጀው ቅጽ መሰረት የዓይን፣ የጆሮ፣ የእጅ፣ የእግር እና ባለሞተር ተሽከርካሪ ለማሽከርከር ከሚያውክ ሌላ ማንኛውም የጤና እክል ነፃ መሆኑን የጤንነት ማረጋገጫ ማስረጃ ከስልጠና በፊት ማቅረብ አለበት፤

፪/ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት አመልካቹ የጤና ጉድለት ካለበት የጤና ተቋሙ ለችግሩ መፍትሄ የሚሆን ማሽከርከር የሚችልበትን ማስረጃ ጨምሮ ሊሰጠው ይችላል፥

## ፯. ፍቃድን ስለማገድ

የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለማግኘት ስልጠና የሚወስድ ማንኛውም ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ እና ፲፫ መሰረት ሊያሟላ የሚገባው ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው

4/ The Ministry or the appropriate organs may make random inspection and check on the competence of trainees who passed examinations by administering reexaminations to them;

5/ Where it is found upon such inspection and check that incompetent trainee is made to pass the examinations, the Ministry or the appropriate organ may take administrative measure against the trainer, licensing organ and the trainee;

6/ The administrative measures to be taken as per Sub-Article (3) and (5) of this Article shall be determined through Directives to be issued by the Ministry.

## 6. Health Requirement

1/ Any applicant for driver's qualification certification license shall, before taking the training, produce a medical certificate from a known medical institution through the forms designated for this purpose by the Ministry or the appropriate organ testifying that he is free of health problems on his eyes, ears, limbs or any other health defects that may make him unfit for driving;

2/ Where the applicant is found to have a health defect of any of those mentioned under Sub-Article (1) of this Article, the medical institution so certifying may also issue alternative solutions based on which the applicant may be able to drive a motor vehicle.

## 7. Suspension of License

Without prejudice to the mandatory requirements of Articles 12 and 13 of the Proclamation that shall be met for any person to qualify for a driving license;

Scanned by CamScanner

፩/ሰልጣኙ የሚያቀርበው ማስረጃ ትክክለኛነቱ የሚያጠራጥር ሆኖ ከተገኘ ሰልጣኙ የማስረጃውን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል እስከሚያቀርብ ድረስ ወይም ቅጣት ተጥሎበት ከሆነም የተጣለበትን ቅጣት እስከሚያጠናቅቅ ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እንዳያወጣ ይታገዳል፡፡

፪/ ማንኛውም አሽከርካሪ የአሽከርካሪነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ በሚያሳድስበት ወቅት ያቀረበው ማስረጃ ትክክለኛነት የሚያጠራጥር ሆኖ ከተገኘ የማስረጃው ትክክለኛነት ከሚመለከተው አካል ተረጋግጦ እስከሚቀርብ ድረስ ወይም ቅጣት ተጥሎበት ከሆነም የተጣለበትን ቅጣት እስከሚያጠናቅቅ ድረስ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ይታገዳል፤

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) እና (፪) መሰረት የሚቀርብ ማስረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲያስችል የሚመለከተው አካል ለሚኒስቴሩ ወይም ለፈቃድ ሰጪ አካል መረጃ ይሰጣል፡፡

**፰ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ስለመስጠት**

፩/ ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወደ ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የሚቀየረው በሁለት ዓመት ውስጥ ባለፈቃዱ ያደረሰው የትራፊክ ጥፋት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱ መሰረት የተያዘበት የሪከርድ ነጥብ ከ፲፩ ያልበለጠ ከሆነ ብቻ ነው፤

1/ An applicant shall be suspended from getting a driving license where there is a suspicion as to the genuineness of the supporting documents or where he has been penalized, until such time that he produces evidence as to the genuineness of the documents or the lapse of penalty period, respectively;

2/ The he driving license of a person shall be suspended where, during renewal, there is a suspicion as to the genuineness of the supporting renewal documents or where he has been penalized, until such time that he produces evidence as to the genuineness of the documents or the lapse of penalty period, respectively;

3/ The concerned organ shall provide evidence as per Sub-Article (1) and (2) of this Article; as to the genuineness of the documents to the Ministry or the appropriate organ in the latter's effort to identify whether the documents are genuine or not.

**8. Issuance of Drivers Qualification Certification License**

1/ Holder of a temporary driver's qualification certification license may be issued with the permanent license only after two years during which period the points recorded for traffic offences as per Road Transport Traffic Control Council of Ministers (Amendment) Regulation No. 395/2017 do not exceed eleven points;

Scanned by CamScanner

፪/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ወደ ቋሚ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሊቀየርለት ያልቻለ እንደሆነ እና ባለፈቃዱ ያደረሰው የትራፊክ ጥፋት የሪከርድ ነጥብ ከ፲፪ እስከ ፲፭ ሲሆን ጊዜያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ ስለሚኖረው ውጤት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ምክንያት በተራዘመው ጊዜ ውስጥ በማሽከርከሩ የትራፊክ አደጋ ወይም ጥፋት ሪከርዱ ከ፲፮ ነጥብ በላይ የሆነ እንደሆነ የተሰጠው ጊዚያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰረዛል፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለፈቃድ በድጋሚ የተግባር እና የንድፍ ሃሳብ ፈተና ወስዶ ብቃቱ ሲረጋገጥ ጊዚያዊ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

፱. <u>የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድን ስለመተካት</u>

፩/ ማንኛውም የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ባለቤት በማንኛውም አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ከጣለ ከመደበኛው የእድሳት ክፍያ ሶስት እጥፍ የምትክ አገልግሎት ክፍያ እንዲከፍል ተደርጎ ምትክ ይሰጠዋል፤

፪/ የምትክ አገልግሎቱ የተጠየቀው ለሶስተኛ ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ምትክ የሚሰጠው ከመደበኛው የእድሳት ክፍያ አምስት እጥፍ የሆነ ክፍያ በማስከፈል ነው፡፡

2/ Situations where the points recorded for traffic offences as mentioned under Sub-Article (1) of this Article are twelve to fifteen, due to which the temporary license couldn't be replaced with a permanent license shall be governed by directives to be issued by the Ministry;

3/ where the temporary license couldn't be replaced with the permanent one as per Sub-Article (2) of this Article; and where the points recorded for traffic offences by the holder of the temporary license during the extended period exceed 16 points, the temporary license itself shall be suspended;

4/ A person whose temporary license has been so suspended as per Sub-Article (3) of this Article may only be issued with a temporary license after passing re examination both for theoretical and practical examinations.

9. **<u>Replacement of Drivers Qualification Certification License</u>**

1/ Any holder of driver's qualification certification license who has lost the license twice in a year may be issued with a replacement of driver's qualification certification license only after payment of a price of three fold of the renewal fee;

2/ Where a replacement is requested for a third times or more, a replacement may be issued only after the payment of five fold of the renewal fee.

Scanned by CamScanner

**፲. የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ጸንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ እና ስለዕድሳት**

፩/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ከአንድ ምድብ ወደ ሌላ ምድብ ወይም ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ምድብ የሚለውጥ አሽከርካሪ የሚቀየረው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የእድሳት ጊዜው ያላለፈበት መሆን አለበት፤ ሆኖም ጊዜው ያለፈ ከሆነ በቅድሚያ የሚቀየረውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ማሳደስ አለበት፤

፪/ ማንኛውም የጸና የውጭ ሀገር ወይም ኢንተርናሽናል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያለው አሽከርካሪ ኢትዮጵያ ውስጥ ተሽከርካሪ ማሽከርከር የሚፈቀድለት በአዋጁ መሠረት ፈቃዱን ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዕለት ቀጣዩ ቀን ጀምሮ ባሉት አርባ አምስት ቀናት ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ካስቀየረ ወይም ፈቃዱን ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው አካል ዘንድ ቀርቦ ካስመዘገበ ብቻ ነው፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት የጸና የውጭ ሀገር ወይም ኢንተርናሽናል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ኢትዮጵያ ውስጥ መጠቀም የሚፈልግ አሽከርካሪ በቅድሚያ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን ትክክለኛነት ከወሰደበት ሀገር ኤምባሲ እና ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አረጋግጦ ማቅረብ አለበት፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተደነገገውን ድንጋጌ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም አሽከርካሪ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ (ማሻሻያ) ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱ « ሠንጠዥ ለ » መሠረት የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳይኖረው እንዳሽከረከረ ተቆጥሮ ይቀጣል፡፡

**10. Validity and Renewal of Drivers Qualification Certification License**

1/ A holder of driver's qualification certification license intending to change the license from one category to the other or to upgrade from a lower to a higher grade my only do so where the validity period of the license he is holding hasn't expired; where, however, the validity period of the license he is holding has already expired, he shall first renew it;

2/ A holder of valid foreign or international driving license may only be allowed to drive motor vehicles using such licenses in Ethiopia where, as stipulated in the Proclamation, he has been issued with the equivalent category of Ethiopian driving license or where he has his foreign or international license registered in Ethiopia within 45 days from the next day of his arrival at the Ministry or the appropriate organ;

3/ A holder of a valid foreign or international driving license intending to use it in Ethiopia as stated under Sub-Article (2) of this Article shall first certify it at the Embassy of the country of issue and the Ministry of Foreign Affairs of Ethiopia;

4/ Any driver found in contravention of the provisions of Sub-Article (2) of this Article shall be considered driving without a license and shall be penalized in accordance with "Schedule B" of the Road Transport Traffic Control Council of Ministers Regulation No. 395/2017 (As Amended);

Scanned by CamScanner

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጸና የውጭ ሃገር ወይም ኢንተርናሽናል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኖሮት ፈቃዱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ሳያስቀይር ወይም ሳያስመዘግብ የአርባ አምስት ቀን የጊዜ ገደቡ ያለፈበት አሽከርካሪ ከአርባ አምስቱ ቀናት በኋላ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው አካል የሚወሰነውን አስተዳደራዊ ቅጣት ከፍሎ ፈቃዱን ሊያስቀይር ወይም አስመዝግቦ ሊገለገልበት ይችላል፤

፮/ የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱን የአገልግሎት ጊዜው ካበቃ በኋላ ባሉት አስራ ሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሳያሳድስ የቀረ ማንኛውም አሽከርካሪ እንደ አዲስ የንድፈ ሀሳብና የተግባር ፈተና ተፈትኖ ብቃቱ ሲረጋገጥ የያዘው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይታደስለታል፡፡

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፩. የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩/ የባለሞተር ተሽከርካሪ አሽከርካሪዎች መንጃ ፈቃድ ደንብ ቁጥር ፫፻፷፪/፲፱፻፷፩ እና የባለሞተር ተሽከርካሪዎች አሽከርካሪ መንጃ ፈቃድ ለማሻሻል የወጣ ደንብ ቁጥር ፵፩/፲፱፻፸፮ በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

፪/ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ውስጥ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለውም፡፡

5/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (4) of this Article, a holder of a valid foreign or international driving license who failed to comply with the provisions of Sub-Article (2) of this Article shall be allowed to have his license converted to the equivalent category of Ethiopian driving license or have it registered within six months from the lapse of the 45 days, provided he pays the administrative penalty that may be determined by the Ministry or the appropriate organs;

6/ A holder of any driving license, who failed to renew the license within twelve months after the date of expiry of the validity period, shall only be issued with a renewed license after passing both theoretical and practical examinations.

## PART THREE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 11. Repealed and Inapplicable Laws

1/ Motor Vehicle Operator License Regulation No. 362/1969 and Motor Vehicle Operator License (Amendment) Regulation No. 41/1976 are here by repealed.

2/ Any Regulation, Directive or practice that contradicts with the Provisions of this Regulation shall not be applicable for matters covered herein.

Scanned by CamScanner

**፲፪. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፫. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፯ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ጠቅላይ ሚኒስትር**

**12. <u>Power to Issue Directives</u>**

The Ministry may issue Directive for the proper implementation of this Regulation.

**13. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall come in to force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 16th March, Day of, 2022**

**ABIY AHMED (Dr.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned by CamScanner